# የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማስተማሪያ ቋንቋ ለምን አማርኛ አይሆንም ?

ታከለ ታደሰ

## 1. 0 ስለ ጥያቄው አነሳስ

በአሁኑ ጊዜ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ለማግኘት ወደ ዩኒቨር ሲቲው የሚገቡት ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ችሎታ ወደታች እያሽቆ ለቆለ መምጣቱ ጉልህ ነው። ለዚህም የመጀመሪያዎቹ ምስክሮች በዩኒቨርሲቲው በቋንቋዎች ተቋም ውስጥ በውጭ ቋንቋዎች ክፍል እንግሊዝኛ የሚያስተምሩት መምህራን ናቸው ። መምህራኑ የመጀመሪ ያና የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎችን በሚያስተምሩበት ጊዜ አብዛኞቹ ተማሪዎች አንድ ቀላል አረፍተ ነገር እንኳን በእንግሊዝኛ ለመጻፍ የማይችሉ መሆናቸውን ከመረዳታቸውም በላይ ተማሪዎቹ ለመለማ መጃ እንዲሆኑ የሚጽፏቸውን የእንግሊዝኛ ድርሰቶች በእንግሊዝኛ ችሎታቸው ማነስ ምክንያት ለማረም በጣም አስቸጋሪና ጊዜ አባካኝ መሆኑን ይናገራሉ ። ሌሎቹን የትምህርት ዓይነቶች የሚያስተምሩት መምህራንም ቢሆኑ ተማሪዎቹ እንግሊዝኛ ባለመቻላቸው ምክንያት የሚፈለገውን ሃሳብ በትክክል ለመግለጽም ሆነ ሲገለጽላቸውም ለመ ረዳት የማይችሉ መሆናቸውን ይጠቁማሉ ። ለምሳሌ በቋንቋዎች ተቋም የሚሰጡትን አንዳንድ የሥነ ልሳን ትምህርቶች በሚማሩበት ጊዜ አን ዳንዶቹ ተማሪዎች አፍ አውጥተው እኛ ሃሳቡ እያለን በእንግሊዝኛ ለመ ግለጽ ስለሚያቅተን በአማርኛ እንድንገልጸው ይፈቀድልን የሚሉ አሉ ።

እነዚህና ሌሎችም ምክንያቶች የዩኒቨርሲቲው የማስተማሪያ ቋንቋ ለምን አማርኛ አይሆንም? የሚለውን ጥያቄ እንዳነሳ ገፋፉኝ ።

የትምህርት ሚኒስቴርም አማርኛ እስከ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ድረስ የማስተማሪያ ቋንቋ እንደ ሚሆን በረጅም ጊዜ ዕቅዱ ውስጥ አስገብ ቶታል ። እንግዲህ እንዲህ ያለ ዕቅድ ካለ በከፍተኛ ደረጃ በአማርኛ የማስተማሩ ተግባር ከመጀመሩ በፊት አስቀድሞ ጥናት ማድረጉ ሥራው ሲጀመር ሊገጥሙ የሚችሉትን ችግሮች ለማወቅ ይረዳል ። በተ ለይ የዩኒቨርሲቲ ደረጃ ትምህርት ለምን በአማርኛ ሊሰጥ እንዳል ቻለ ለማወቅ ከዚህ በፊት ምንም የተደረገ ጥናት ስለሌለ ይህ ጥናት ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ለወደፊቱ መደረግ ለሚገባቸው ጥናቶች እንደመነሻ ሊያገለግል ይችላል ።

## 2. የጥናቱ ዘዴ

በመጀመሪያ ጥናቱ የተጀመረው በዩኒቨርሲቲው ባሉት ፋኩልቲዎች ውስጥ የሚገኙትን የየክፍል ኃላፊዎችን በቃል በማነጋገር ነበር ። በዕቅ ዱም መሠረት በመጀመሪያ የሥነፍጥረት /ሳይንስ/ ፋኩልቲ የስድስት ክፍል ሃላፊዎች በቃል ተጠይቀው የሰጡት መልስ ተስተካክሎ ተመዘገበ።

# የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማስተማሪያ ቋንቋ ለምን አማርኛ አይሆንም ?

ታከለ ታደሰ

## 1.0 ስለ ጥያቄው አነሳስ

በአሁኑ ጊዜ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ለማግኘት ወደ ዩኒቨር ሲቲው የሚገቡት ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ችሎታ ወደታች እያሽቆ ለቆለ መምጣቱ ጉልህ ነው። ለዚህም የመጀመሪያዎቹ ምስክሮች በዩኒቨርሲቲው በቋንቋዎች ተቋም ውስጥ በውጭ ቋንቋዎች ክፍል እንግሊዝኛ የሚያስተምሩት መምህራን ናቸው ። መምህራኑ የመጀመሪ ያና የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎችን በሚያስተምሩበት ጊዜ አብዛኞቹ ተማሪዎች አንድ ቀላል አረፍተ ነገር እንኳን በእንግሊዝኛ ለመጻፍ የማይችሉ መሆናቸውን ከመረዳታቸውም በላይ ተማሪዎቹ ለመለማ መጃ እንዲሆኑ የሚጽፏቸውን የእንግሊዝኛ ድርሰቶች በእንግሊዝኛ ችሎታቸው ማነስ ምክንያት ለማረም በጣም አስቸጋሪና ጊዜ አባካኝ መሆኑን ይናገራሉ ። ሌሎቹን የትምህርት ዓይነቶች የሚያስተምሩት መምህራንም ቢሆኑ ተማሪዎቹ እንግሊዝኛ ባለመቻላቸው ምክንያት የሚፈለገውን ሃሳብ በትክክል ለመግለጽም ሆነ ሲገለጽላቸውም ለመ ረዳት የማይችሉ መሆናቸውን ይጠቁማሉ ። ለምሳሌ በቋንቋዎች ተቋም የሚሰጡትን አንዳንድ የሥነ ልሳን ትምህርቶች በሚማሩበት ጊዜ አን ዳንዶቹ ተማሪዎች አፍ አውጥተው እኛ ሃሳቡ እያለን በእንግሊዝኛ ለመ ግለጽ ስለሚያቅተን በአማርኛ እንድንገልጸው ይፈቀድልን የሚሉ አሉ ።

እነዚህና ሌሎችም ምክንያቶች የዩኒቨርሲቲው የማስተማሪያ ቋንቋ ለምን አማርኛ አይሆንም? የሚለውን ጥያቄ እንዳነሳ ገፋፉኝ ።

የትምህርት ሚኒስቴርም አማርኛ እስከ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ድረስ የማስተማሪያ ቋንቋ እንደ ሚሆን በረጅም ጊዜ ዕቅዱ ውስጥ አስገብ ቶታል ። እንግዲህ እንዲህ ያለ ዕቅድ ካለ በከፍተኛ ደረጃ በአማርኛ የማስተማሩ ተግባር ከመጀመሩ በፊት አስቀድሞ ጥናት ማድረጉ ሥራው ሲጀመር ሊገጥሙ የሚችሉትን ችግሮች ለማወቅ ይረዳል ። በተ ለይ የዩኒቨርሲቲ ደረጃ ትምህርት ለምን በአማርኛ ሊሰጥ እንዳል ቻለ ለማወቅ ከዚህ በፊት ምንም የተደረገ ጥናት ስለሌለ ይህ ጥናት ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ለወደፊቱ መደረግ ለሚገባቸው ጥናቶች እንደመነሻ ሊያገለግል ይችላል ።

## 2. የጥናቱ ዘዴ

በመጀመሪያ ጥናቱ የተጀመረው በዩኒቨርሲቲው ባሉት ፋኩልቲዎች ውስጥ የሚገኙትን የየክፍል ኃላፊዎችን በቃል በማነጋገር ነበር ። በዕቅ ዱም መሠረት በመጀመሪያ የሥነፍጥረት /ሳይንስ/ ፋኩልቲ የስድስት ክፍል ሃላፊዎች በቃል ተጠይቀው የሰጡት መልስ ተስተካክሎ ተመዘገበ።

ከቃል ጥያቄ ይልቅ የጽሑፍ ጥያቄ የበለጠ ተጨባጭነት ይኖረዋል የሚል አስተሳሰብ ስለቀረበ ጥናቱን በመጀመሪያው እንደታሰበው ሳይሆን መጠይቅ በማዘጋጀት በጽሑፍ እንዲካሄድ ተደረገ ። በዚህኛው እቅድም መሠረት መጠይቅ ተዘጋጅቶ በዩኒቨርሲቲው በማስተማር ላይ ለሚገኙት መምህራን ተሰጠ። መልሱም ከተሰበሰበ በኋላ ተጠና ቅሮና ተገምግሞ ቀረበ ። በመጨረሻ እንደተባለው ጥናቱ የተካሄደው በመጠይቅ ቢሆንም የመጀመሪያው ስድስቱ የሳይንስ ፋኩልቲ የየክ ፍል ኃላፊዎች የሰጡትም መልስ አልተጣለም ። በመጠይቁ ከተሰጡት መልሶች ጋር ተዛምዶ የመጨረሻውን የጥናቱን ግኝት ለመወሰን ረድቷል። ሌላው የጥናቱን ግኝት ሊያጠናክረው የቻለው ነገር ደግሞ አንዳንድ መጠይቁን ሞልተው የመለሱ በነገሩ ልዩ ስሜት ያደረባቸው መምህራን በመጠይቁ ከተሰጧቸው ጥያቄዎች በተጨማሪ እራሳቸው የሰጧቸው ሰፋ ያሉ አስተያየቶች ናቸው ። እነዚህ የተጠቀሱት አስተያ የቶችና የሳይንስ ፋኩልቲ የየክፍል ኃላፊዎች የሰጧቸው አስተያየቶች በመጠይቁ አማካኝነት ከተገኙት መልሶች ጋር ተመሳሳይነት ስላላቸው በመጠይቁ የተገኙትን የመጨረሻ ውጤቶች በጣም ያጠናክሩ መሆ ናቸውን አንባቢ እንዲገነዘበው ያስፈልጋል ።

በተጨማሪ ምንም እንኳን በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በየፋኩልቲዎቹ በማስተማር ላይ የሚገኙት መምህራን ብዙ ቢሆኑም ፈቃደኛ ሆነው መጠይቁን ሞልተው የመለሱት ከብዛታቸው ጋር አይመጣጠንም ። ቢሆንም ለመጠይቁ መልስ የሰጡት ከመቶ በላይ በመሆናቸው በመጠ ይቁ አማካኝነት የሚገኘው ፍሬ ነገር ለተነሣው ጥያቄ ተጨባጭ ፍንጭ ያለው መልስ የሚሰጥ ለመሆኑ በእስታቲስቲክስ አዋቂዎች ተመር ምሮ በካይ እስቱርድ ተመዝኖ በመጠይቁ አማካኝነት በተገኙት መልሶች ላይተመስርቶ የሚሰጠው ማናቸውም ውሳኔ ትክክል መሆኑን መስክረዋል ።

## ፫. ፩ የጥናቱ ግኝት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚሰጡትን የትምህርት ዓይነቶች ሁሉ በአማርኛ ማስተማሩን በማዕረግም ሆነ በፋኩልቲ ከማይቃወመው የሚቃወመው ላቅ ብሎ ተገኝቷል። በማዕረግ ሲታይ ከምሩቅ ረዳት እስከ ተባባሪ ፕሮፌሰር ድረስ ያሉት 70% የሚሆኑት ተቃውመዋል ። ከነዚህ ውስጥ ምሩቅ ረዳቶች ከፍተኛውን ተቃውሞ 80% ሲያሳዩ ዝቅተኛውን ተቃውሞ 60% ያሳዩት ረዳት ፕሮፌሰሮች ናቸው ።

በፋኩልቲ ደረጃ በአጠቃላይ 63% ተቃውመዋል ። ከፋኩልቲዎች ከፍተኛውን ተቃውሞ ያሳየው 78% የስነፍጥረት ፋኩልቲ ሲሆን

ውን ተቋውሞ ያሳየው 35.4% የቋንቋዎች ተቋም ነው ፡፡64.6% ት የቋንቋዎች ተቋም መምህራን ሃሳቡን ይደግፋሉ ማለትነው።

ፊታልሀኖ ፍል በኩል የተመለከትን እንደሆነ ከስነፍጥረት ፋኩልቲ ኖሬ ፊ ክፍል መቶ በመቶ ሃሳቡን ሲቃወም የሂሣብ ክፍል ደግሞ ኗሐሠ ሃሣቡን ይደግፋል። እንዲሁም በሕክምና ፋኩልቲ የኀብረተ ፱፲ ፲፱ኗ ክፍል ሃሣቡን መቶ በመቶ ሲደግፍ የፊዚዮሎጂ ክፍል ደግሞ መቶ በመቶ ይቃወማል። ከሶሻል ሳይንስ የታሪክ፣ የጂኦግራ ፊና የሥነ አድሚኒስትሬሽን ክፍሎች መቶ በመቶ ሲቃወሙ የፖለቲካ የተግባራዊ ኅብረተሰብ ጥናትና የፍልስፍና ክፍሎች ለመጠይቁ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል ፡፡ /ገበታ 1 ይመልከቱ ፡፡ /

የሕግ ፋኩልቲ መቶ በመቶ የደገፈ ሲሆን መጠይቁን ሞልተው ከመለሱት አራት መምህራን መካከል በፍርድ ቤቶች የሚሰራው ሥራ የሚካሄደው በአማርኛ ስለሆነ የሕግ ፋኩልቲን ትምህርት እንዲያ ውም በአማርኛ ማስተማር ግዴታ መሆን ነበረበት ያሉ አሉ ፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚሰጡትን የትምህርት ዓይነቶች ሁሉ በአማርኛ ማስተማሩን እንቃወማለን ያሉትም ሆነ አንቃወምም ያሉት የዩኒቨርሲቲው ትምህርት አሁንም በአማርኛ የማይሰጥበትን ምክንያት እንዲጠቁሙ ለምርጫ ከቀረቡላቸው አምስት ምክንያቶች ውስጥ በማዕረግም ሆነ በፋኩልቲ ከፍተኛ ብልጫ ሰጥተው የመረጡት ምክንያት ትምህርቱ በአማርኛ ከመሰጠቱ በፊት በቂ ዝግጅት ስለሚጠ ይቅ ነው የሚለውን ነው ፡ በማዕረግ ስንመለከት የያንዳንዱ መምህር ችሎታችንትና ፍላጐት ማጣት ነው የሚለውን ከምሩቅ ረዳት እስከ ሌክቸረር ያሉት ጥቂቶች ሲመርጡት ከሌክቸረር በላይ ያሉት አልመረ ጡትም ፡፡ በፋኩልቲ ደረጃ የቋንቋ ተቋምና የሥነ ትምህርት ፋኩልቲ ዎች ብቻ መርጠውታል ፡፡ ከበላይ አካል ውሳኔ ባለመሰጠቱ ነው የሚለውን ምክንያት ምሩቅ ረዳቶችና ተባባሪ ፕሮፌሰሮች ጨርሰው ሲተዉት ሌሎች መርጠውታል ፡፡

በኔ በኩል ይቻላል የሚለውን ሌክቸረሮችና ከዚያ በታች ያሉት ብቻ ሲመርጡት ከፋኩልቲዎች የቋንቋ ተቋም ብቻ መርጦታል ፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚሰጠውን ትምህርት በአማርኛ ማስተማሩን የሚቃወሙት መምህራን የሚቃወሙበትን ምክንያት እንዲገልጹባቸው በዝርዝር ከተሰጣቸው አስር ምክንያቶች ውስጥ በማ ዕረግም ሆነ በፋኩልቲ ከፍተኛውን ቍጥር በመስጠት የሚከተሉትን ሁለት ምክንያቶች መርጠዋል ፡፡

## ጥያቄ 1 በፋኩልቲ

28. 5

| | ሶሻል ሳይንስ | ሳይንስ | ትምህርት | ህክምና | መሃንዲስ | የቋንቋ ቲቋም | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| እቃወማለሁ | 16 | 33 | 4 | 15 | 2 | 11 | 81 |
| አልቃወምም | 9 | 5 | 2 | 6 | — | 10 | 32 |
| እንዲያውም እደግፋለሁ | — | 4 | 1 | — | — | 10 | 15 |
| | 25 | 42 | 7 | 21 | 2 | 31 | 128 |

## ጥያቄ 1 በክፍል

## ህክምና

8. 1

| | አናቶሚ | የኅብረተ ስብ ጤና | የውስጥ ህክምና | ሜዲካል | ፋርማ ኮሎጂ | ፊዚዩ ሎጂ | የሕጻና ሕክምና | ነብሳትና ህዋሳት | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| እቃወማለሁ | 2 | — | 2 | 1 | 1 | 3 | 2 | 1 | 12 |
| አልቃወምም | 1 | 2 | 1 | 1 | — | — | — | — | 5 |
| እንዲያውም እደግፋለሁ | — | — | — | — | — | — | — | — | 0 |
| | 3 | 2 | 3 | 2 | 1 | 3 | 2 | 1 | 17 |

ጥያቄ 1

9. 1

## ትምህርት

| | የቴክኒክና መምህራን ማሰልጠኛ | የ1ኛና የ2ኛ ደረጃ ት. | የጥናት ምርመራ | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|
| እቃወማለሁ | 3 | — | 1 | 4 |
| አልቃወምም | — | 2 | — | 2 |
| እንዲያውም እደግፋለሁ | — | — | 1 | 1 |
| | 3 | 2 | 2 | 7 |

## ጥያቄ 1 በፋኩልቲ

28. 5

| | ሶሻል ሳይንስ | ሳይንስ | ትምህርት | ህክምና | መሃንዲስ | የቋንቋ ቲቋም | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| እቃወማለሁ | 16 | 33 | 4 | 15 | 2 | 11 | 81 |
| አልቃወምም | 9 | 5 | 2 | 6 | — | 10 | 32 |
| እንዲያውም እደግፋለሁ | — | 4 | 1 | — | — | 10 | 15 |
| | 25 | 42 | 7 | 21 | 2 | 31 | 128 |

## ጥ ያ ቄ 1 በ ክ ፍ ል
## ህ ክ ም ና

8. 1

| | አናቶሚ | የኅብረተ ስብ ጤና | የውስጥ ህክምና | ሜዲካል | ፊርማ ኮሎጂ | ፊዚዮ ሎጂ | የሕጻና ሕክምና | ነብሳትና ህዋሳት | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| እቃወማለሁ | 2 | — | 2 | 1 | 1 | 3 | 2 | 1 | 12 |
| አልቃወምም | 1 | 2 | 1 | 1 | — | — | — | — | 5 |
| እንዲያውም እደግፋለሁ | — | — | — | — | — | — | — | — | 0 |
| | 3 | 2 | 3 | 2 | 1 | 3 | 2 | 1 | 17 |

ጥ ያ ቄ 1

9. 1

## ት ም ህ ር ት

| | የቴክኒክና መምህራን ማሰልጠኛ | የ1ኛና የ2ኛ ደረጃ ት. | የጥናት ምርመራ | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|
| እቃወማለሁ | 3 | — | 1 | 4 |
| አልቃወምም | — | 2 | — | 2 |
| እንዲያውም እደግፋለሁ | — | — | 1 | 1 |
| | 3 | 2 | 2 | 7 |

ጥያቄ 1

**መሃንዲስ**

| | ሲቪል መሃንዲስ | ሜካኒካል መሃንዲስ | ኤሌክትሪክ መሃንዲስ | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|
| እቃወማለሁ | — | 2 | — | 2 |
| አልቃወምም | — | — | — | 0 |
| እንዲያውም እደግፋለሁ | — | — | — | 0 |
| | 0 | 2 | 0 | 2 |

**ጥ ያ ቄ 2 በ ማ ዕ ረ ግ**

10. 2

| | ተባባሪ ፕሮፌሰር | ረዳት ፕሮፌሰር | ሌክቸረር | ረዳት ሌክቸረር | ምሩቅ ረዳት | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | — | — | 3 | 1 | 1 | 5 |
| ለ | — | 2 | 3 | 3 | 3 | 8 |
| መ | 2 | 3 | 8 | 3 | 3 | 19 |
| ረ | 10 | 17 | 27 | 31 | 13 | 98 |
| ሰ | — | — | 2 | 1 | 1 | 4 |
| | | | | — | | |
| | 12 | 22 | 43 | 39 | 18 | 134 |

**ጥ ያ ቄ 2 በ ፋ ኩ ል ቲ**

28. 4

| | ሶሻል ሳይንስ | ሥነ ፍጥረት | ትምህርት | ሕክምና | መሃንዲስ | የቋንቋ ተቋም | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | — | — | 1 | — | — | 5 | 6 |
| ለ | 2 | 2 | 1 | — | — | 5 | 10 |
| መ | 4 | 7 | — | 5 | — | 3 | 19 |
| ረ | 20 | 36 | 5 | 13 | 2 | 27 | 103 |
| ሰ | — | — | — | — | — | 3 | 3 |
| | | | | | | | |
| | 26 | 45 | 7 | 18 | 2 | 43 | 141 |

ቅድተኛ ድምፅ ካገኙት ከሁለቱ ምክንያቶች ሌላ በሦስተኛ
መረጡትን ምክንያቶች ስንመረምር መጀመሪያ በማዕረግ
ራቸው ተባባሪ ፕሮፌሰሮች ብቻ ሁለት ምክንያቶች በሦስ
መርጠዋል ። ምክንያቶቹም

፩ በሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች በውጭ ቋንቋዎች በብዛት ተጽፈው የሚገኙትን መጻሕፍት ወደ አማርኛ ለመተርጐም ፍጹም የማይቻል በመሆኑ ነው *

2. የአማርኛ ቋንቋ ዘመናዊ ወይንም የቴክኖሎጂ ጽንሰ ሃሳቦ ችን ለመግለጽ የማይችል ቋንቋ መሆኑን በመገንዘቤ ነው የሚሉትናቸው * *

ረዳት ፕሮፌሰሮች ለጊዜው ፍጹም የማይቻል በመሆኑ ነው የሚለውን በሦስተኛነት ሲመርጡ ሌክቸረሮች ደግሞ ተባባሪ ፕሮፌሰሮች የመረጧቸውን ከላይ የተጠቀሱትን ሁለቱን ምክንያቶችና አማርኛ የኢትዮጵያውያን ሁሉ አፍ መፍቻ ቋንቋ ባለመሆኑ ነው የሚለውን ጨምረው ሦስቱንም በሦስተኛነት መርጠዋል ። ረዳት ሌክቸረሮ ችም ይህንኑ ምክንያትና ረዳት ፕሮፌሰሮች የመረጡትን ለጊዜው ፍጹም የማይቻል በመሆኑ ነው የሚለውን እንደ ሦስተኛ ምክንያት መርጠዋል። ምሩቅ ረዳቶች ሦስተኛ አድርገው የመረጡት የአማርኛ

---

* ቀደም ሲል በተሰጠው የግርጌ ማስታወሻ እንደተመለከተው ይህም አስተሳሰብ የቋ ንቋን ዕድገት ካለመረዳት የመነጨ ነው ።

* * ለጊዜው እንጂ ይህም ቢሆን የአማርኛ የተፈጥሮ ባሕርይ ሊሆን አይችልም ።

ቋንቋ ዘመናዊ ወይንም የቴክኖሎጂ ዕንስ ሃሣቦችን ለመግ
ይችል ቋንቋ መሆኑን በመገንዘብ ነው የሚለውን ምክንያት
በፋኩልቲ ደረጃ ስንመለከት የሥነፍጥረትና የሕክምና ፋኩ
በሶስተኛነት የመረጡት ምክንያት ለጊዜው ፍጹም የማይቻ
ሆኑ ነው የሚለውን ሲሆን የሶሻል ሳይንስ ፋኩልቲ አማርኛ የአ
ውያን ሁሉ አፍ መፍቻ ቋንቋ ባለመሆኑ ነው ። የአማርኛ ቋንቋ
ወይንም የቴክኖሎጂ ዕንስ ሃሣቦችን ለመግለጽ የማይችል ቋን
ኑን በመገንዘብ ነው እና ለጊዜውም ፍጹም የማይቻል መሆኑ
ገንዘቤ ነው የሚሉትን ምክንያቶች መርጠዋል። ከዚህ ቀጥሎ
እንደግፋለን የሚሉት መምህራን የሰጧቸውን ምክንያቶች እንመለ
ከታለን ።

የዩኒቨርሲቲው ትምህርት በአማርኛ ቢሰጥ አንቃወምም የሚሉ
ትና እንዲያውም እንደግፋለን የሚሉት በአንደኛ ደረጃ የመረጡት
ምክንያት ተማሪው ትምህርቱን በእንግሊዝኛ ከሚማረው ይልቅ በአማ
ርኛ ቢማረው የበለጠ ሊረዳው ስለሚችል ነው የሚለውን ነው ። በፋኩ
ልቲ ደረጃም ይኸው ምክንያት በአንደኛነት በአብዛኞቹ ሲመረጥ የሳይ
ንስ ፋኩልቲ ግን በአንደኛነት የመረጠው ምክንያት ለወደፊቱ ብዙ
ሰው በራሱ ጥረት ዕውቀቱን ለማስፋፋት የሚችልበትን መንገድ
ስለሚከፍት ነው የሚለውን ነው ። ይህ ምክንያት በአጠቃላይ በሁለተ
ኛነት የተመረጠ ሲሆን በአጠቃላይ በሦስተኛነት የተመረጠው ደግሞ
በየትምህርቱ ዓይነቶች በአማርኛ የሚጻፉት እየበዙ እንዲሄዱ ስለሚ
ረዳ ነው የሚለው ነው ። ለተጨማሪ መረጃ እነዚህን ውጤቶች የሚ
ያሳዩትን ገበታዎች ይመልከቱ ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚሰጠውን ትምህርት ለምን በአማርኛ
አናስተምርም ለሚለው ጥያቄ ወዲያውኑ ሊሰጥ የሚችለው መልስ

ግልጽ መስሎ ቢታይም የብዙ ሰዎችን መልስና አስተሳሰብ አመዛዝኖና ጨምቆ የሚሰጠው መልስ በራስ አስተሳሰብ ወዲያው ከሚሰጠው መልስ የበለጠ ተጨባጭና ጠቃሚ እንደሚሆን እሙን ነው ። በዚሁ አስተሳሰብ መሠረት የብዙ መምህራንና የሥነ ፍጥረት ፋኩልቲ የክፍል ኃላፊዎችን ሃሣብ በመሰብሰብ የተገኘው ሃሣብ የሚከተሉትን የመጨረሻ ውጤቶች አስገኝቷል።

፩. በአጠቃላይ ለመጠይቁ መልስ የሰጡት የዩኒቨርሲቲው መምህራን ትምህርቱ በአማርኛ መሰጠቱን ይቃወማሉ ። ከሚቃወሙበትም ምክንያቶች አውራዎቹ አማርኛ በቂ ዘመናዊ ቃላት ስለሌሉትና ለተከታታይ ንባብ በአማርኛ የተጻፉ መጻሕፍት ስለሌሉ ነው የሚሉት ናቸው ። የሳይንስ ፋኩልቲ የየክፍል ሃላፊዎች በቃል የሰጡትም መልስ ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ ነው ። በመምህራኑ መጠይቅ መልስና በሳይንስ ፋኩልቲ የክፍል ኃላፊዎች የቃል መልስ ልዩነት ያለ መስሎ የሚታይ ነገር ቢኖር እመቃወሙ ላይ ነው ። በመጠይቅ ለመለሱት መምህራን በመጀመሪያ የቀረበው የመቃወም ወይም የመደገፍ የአቋም መግለጫ ሲሆን ለክፍሉ ኃላፊዎች የቀረበ የመጀመሪያ ጥያቄ ግን የክፍሉን ትምህርት በአማርኛ ማስተማር መቻል ወይንም አለመቻሉን ነው ። ለመጠይቁ መልስ ከሰጡት መምህራን አብዛኞቹ በአማርኛ ማስተማሩን የተቃወሙበት ምክንያት በቃላትና በመጻሕፍት እጥረት እንጂ በሌላ ምክንያት አይመስልም። ስለዚህ የቃላትና የመጻሕፍት እጥረት ብቻ የዩኒቨርሲቲውን ትምህርት በአማርኛ እንዳይሰጥ አድርጎታል ማለት ነው ።

፪. እንዲህም ሆኖ በአሁኑ ጊዜ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ባሉት አንዳንድ ክፍሎች የሚሰጠውን ትምህርት በአማርኛ ማስተማር የሚቻል መሆኑን ፍንጭ ሰጥቷል ። ለምሳሌ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በስተቀር በቋንቋዎች ተቋምና በሕግ ፋኩልቲ የሚሰጠውን ትምህርት በአማርኛ ማስተማር ይቻላል ማለት ነው ። እንዲሁም በሥነ ፍጥረት ፋኩልቲ በሂሣብ ፤ በፊዚክስና በሥነ ምድር ክፍሎች በአማርኛ ማስተማር የመጀመሩ ዝንባሌ ሲታይ በሕክምና ፋኩልቲ በኅብረተሰብ ጤና ክፍል በኩል የዚሁ ሁኔታ መኖሩ ፍንጭ ይታያል ።

## ገበታ 2
## ጥያቄ 3 በማዕረግ

23.2

| | ተባባሪ ፕሮፌሰር | ረዳት ፕሮፌሰር | ሌክቸረር | ረዳት ሌክቸረር | ምሩቅ ረዳት | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | — | 3 | 7 | 12 | 3 | 25 |
| ለ | 5 | 11 | 1 | 18 | 10 | 55 |
| መ | 6 | 9 | 13 | 26 | 11 | 65 |
| ረ | 4 | 3 | 7 | 7 | 3 | 24 |
| ሰ | 4 | 5 | 7 | 7 | 6 | 29 |
| ሸ | 1 | 1 | 2 | 8 | 2 | 14 |
| ቀ | — | 2 | — | 1 | 1 | 4 |
| በ | 2 | 8 | 5 | 12 | 5 | 32 |
| ተ | 1 | 1 | — | 2 | 1 | 5 |
| ቸ | 1 | 4 | 3 | 7 | 1 | 16 |
| | 24 | 47 | 55 | 100 | 43 | 269 |

## ጥያቄ 3 በፋኩልቲ

32.4

| | ሶሻል ሳይንስ | ሳይንስ | ትምህርት | ህክምና | መሃንዲስ | የቋንቋ ተቋም | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | 6 | 14 | 1 | 1 | — | 4 | 26 |
| ለ | 8 | 31 | 4 | 12 | — | 4 | 59 |
| መ | 13 | 23 | 3 | 14 | 2 | 13 | 68 |
| ረ | 4 | 9 | 1 | 7 | — | 1 | 22 |
| ሰ | 6 | 14 | 2 | 7 | — | 4 | 33 |
| ሸ | 5 | 8 | — | 1 | — | 1 | 15 |
| ቀ | 1 | 3 | — | — | — | — | 4 |
| በ | 6 | 16 | — | 8 | 1 | 3 | 34 |
| ተ | 1 | 2 | — | 1 | — | — | 4 |
| ቸ | 2 | 10 | — | 3 | — | — | 15 |
| | 52 | 130 | 11 | 54 | 3 | 30 | 280 |

## ጥያቄ 4 በማዕረግ

20.7

| | ተባባሪ ፕሮፌሰር | ረዳት ፕሮፌሰር | ሌክቸረር | ረዳት ሌክቸረር | ምሩቅ ረዳት | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | 3 | 9 | 6 | 8 | 3 | 29 |
| ለ | 1 | 7 | 4 | 7 | 2 | 21 |
| መ | 1 | 5 | 6 | 6 | 3 | 21 |
| ረ | 2 | 5 | — | 5 | 1 | 13 |
| ሰ | — | 4 | — | 2 | 1 | 7 |
| ሸ | 1 | 5 | — | 2 | — | 8 |
| ቀ | 1 | 5 | — | 1 | — | 7 |
| | 9 | 40 | 16 | 31 | 10 | 106 |

## ጥያቄ 4 በፋኩልቲ

14.3

| | ሶሻል ሳይንስ | ሳይንስ | ትምህርት | ህክምና | መሃንዲስ | የቋንቋ ተቋም | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | 3 | 8 | 2 | 3 | — | 13 | 29 |
| ለ | 2 | 6 | — | 2 | — | 11 | 21 |
| መ | 2 | 10 | — | 1 | — | 10 | 23 |
| ረ | 1 | 4 | — | 2 | — | 5 | 12 |
| ሰ | 1 | 5 | — | 1 | — | 1 | 8 |
| ሸ | 2 | 4 | — | 2 | — | 3 | 11 |
| ቀ | 1 | 3 | — | — | — | 2 | 6 |
| | 12 | 40 | 2 | 11 | 0 | 45 | 110 |

፫. አንዳንድ መምህራን በመጠይቁ ወረቀት ላይ በተጨማሪ ከሰጡት አስተያየትና ከሥነ ፍጥረት ፋኩልቲ የየክፍል ኃላፊዎች ከጠቆሙት አስተያየት የተገኘ ሌላ አማራጭ አለ ። ይኸውም አማራጭ ሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች በአንድ ጊዜ በአማርኛ ማስተማር ከመጀመር ይልቅ በአማርኛ ሊሰጡ በሚችሉት እንደ የትምህርቱ ዓይነት በማመዛዘን በቅደም ተከተል መጀመሩ ይሻ ላል የሚል ነው ። ይህ አማራጭ በመጠይቁ ከተገኘው መልስ ጋር ስለሚዛመድ የሚያዋጣ ይመስላል ። የቋንቋ ተቋምና የሕግ ፋኩልቲ ለዚህ አማራጭ ምሳሌዎች ሊሆኑ ይችላሉ ።

፬. ከዚሁ ምንጭ የተገኘው ሌላው አማራጭ ደግሞ በአማርኛ ማስ ተማሩ የትምህርት ቀጠናዎችን እያለፈ በደረጃው ይምጣ የሚለው ነው ። ይኸውም በአንደኛ ደረጃ እንደተጀመረው ዓይነት ወደ ሁለ ተኛ ደረጃም ተሸጋግሮ ከዚያም በመቀጠል ወደ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ይሸጋገር የሚል ነው። ይህኛው አማራጭ ትክክል መስሎ ቢታ ይም በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ግፊት ከሌለ አዝጋሚ ሊሆን ስለሚችል በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ትምህርቱ በአማርኛ ሊሰጥ የሚቻል ከሆነና ከተጀመረ በትምህርት ሚኒስቴር ላይ ከፍተኛ ግፊት ስለሚደርስበትና በአማርኛ የማስተማሩን ተግባር ሊያፋጥነው ስለሚችል ትምህርቱ በሁለተኛ ደረጃ በአማርኛ ባለመሰጠቱ ብቻ የዩኒቨርሲቲውን ትምህርት በአማርኛ ከመስጠት ይታገድ ማለት ትክክል ስለማይሆን ከተቻለ የዩኒቨርሲቲው ትምህርት በአማርኛ የመስጠቱ ተግባር ቢጀመር መልካም ነው ።

## 4. 0 መደምደሚያ

ከቋንቋዎች በስተቀር በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚሰጡትን የትምህርት ዓይነቶች በአማርኛ ለማስተማር ያልተቻለበት ምክንያት የዘመናዊ ቃላትና የመጻሕፍት እጥረት ለመሆኑ በዚህ ጥናት በግልጽ ከታወቀ ይህ ችግር እንዴት ሊፈታ ይችላል? የሚለው ጥያቄ መለጠቁ የማይቀር ነው ።

ከሁለቱ እጥረቶች ለመወጣት ይበልጥ የማያስቸግረው የቃላቱ እጥረት ነው። ነገር ግን የዘመናዊ ቃላት እጥረት የአማርኛ ብቻ ሳይ ሆን በእድገት ወደኋላ የቀሩ አገሮች ቋንቋዎች ሁሉ ችግር መሆኑ መታወቅ አለበት ።

በአማርኛ በኩል ይህንን ችግር ለመወጣት የሚያስችሉ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ናቸው ። ይኸውም ፩/የሥነ ፍጥረት ፋኩልቲ የሥነ መጽሔት

፫. አንዳንድ መምህራን በመጠይቁ ወረቀት ላይ በተጨማሪ ከሰጡት አስተያየትና ከሥነ ፍጥረት ፋኩልቲ የየክፍል ኃላፊዎች ከጠቆሙት አስተያየት የተገኘ ሌላ አማራጭ አለ ። ይኸውም አማራጭ ሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች በአንድ ጊዜ በአማርኛ ማስተማር ከመጀመር ይልቅ በአማርኛ ሊሰጡ በሚችሉት እንደ የትምህርቱ ዓይነት በማመዛዘን በቅደም ተከተል መጀመሩ ይሻላል የሚል ነው ። ይህ አማራጭ በመጠይቁ ከተገኘው መልስ ጋር ስለሚዛመድ የሚያዋጣ ይመስላል ። የቋንቋ ተቋምና የሕግ ፋኩልቲ ለዚህ አማራጭ ምሳሌዎች ሊሆኑ ይችላሉ ።

፬. ከዚሁ ምንጭ የተገኘው ሌላው አማራጭ ደግሞ በአማርኛ ማስተማሩ የትምህርት ቀጠናዎችን እያለፈ በደረጃው ይምጣ የሚለው ነው ። ይኸውም በአንደኛ ደረጃ እንደተጀመረው ዓይነት ወደ ሁለተኛ ደረጃም ተሸጋግሮ ከዚያም በመቀጠል ወደ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ይሸጋገር የሚል ነው። ይህኛው አማራጭ ትክክል መስሎ ቢታይም በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ግፊት ከሌለ አዝጋሚ ሊሆን ስለሚችል በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ትምህርቱ በአማርኛ ሊሰጥ የሚቻል ከሆነና ከተጀመረ በትምህርት ሚኒስቴር ላይ ከፍተኛ ግፊት ስለሚደርስበትና በአማርኛ የማስተማሩን ተግባር ሊያፋጥነው ስለሚችል ትምህርቱ በሁለተኛ ደረጃ በአማርኛ ባለመሰጠቱ ብቻ የዩኒቨርሲቲውን ትምህርት በአማርኛ ከመስጠት ይታገድ ማለት ትክክል ስለማይሆን ከተቻለ የዩኒቨርሲቲው ትምህርት በአማርኛ የመስጠቱ ተግባር ቢጀመር መልካም ነው ።

## 4. 0 መደምደሚያ

ከቋንቋዎች በስተቀር በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚሰጡትን የትምህርት ዓይነቶች በአማርኛ ለማስተማር ያልተቻለበት ምክንያት የዘመናዊ ቃላትና የመጻሕፍት እጥረት ለመሆኑ በዚህ ጥናት በግልጽ ከታወቀ ይህ ችግር እንዴት ሊፈታ ይችላል? የሚለው ጥያቄ መለጠቁ የማይቀር ነው ።

ከሁለቱ እጥረቶች ለመወጣት ይበልጥ የማያስቸግረው የቃላቱ እጥረት ነው። ነገር ግን የዘመናዊ ቃላት እጥረት የአማርኛ ብቻ ሳይሆን በእድገት ወደኋላ የቀሩ አገሮች ቋንቋዎች ሁሉ ችግር መሆኑ መታወቅ አለበት ።

በአማርኛ በኩል ይህንን ችግር ለመወጣት የሚያስችሉ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ናቸው ። ይኸውም ፩/የሥነ ፍጥረት ፋኩልቲ የሥነ መጽሔት

የስያሜ ቡድን በአማርኛ የሥነ ፍጥረት ቃላት የሚሰየሙበትን መንገድ በመፈለግና በመሰብሰብ ላይ ነው ። ፪/በባህልና እስፖርት ጉዳይ ሚኒ ስቴር ሥር የተቋቋመው የቋንቋዎች አካዳሚ ሕጋዊ ሰውነቱ የሚታ ወቅበት አዋጅ ሲታወጅ ከፕሮግራሙ አንዱ የአማርኛ የቃላት ስያሜ ስለሚሆን ከአሁኑ ባጀት እንደሚያዝለትና ሥራው እንዲጀመር እንደሚያደርግ ታውቋል ።

በተጨማሪ ደግሞ ወደፊት የሚቋቋመው የስያሜ ቡድን ወይንም ኮሚቴ የተሰየሙ ቃላት በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲታወቁ ለማድረግ ሆነ ቃላቱን ለመሰየም የሚረዱ ሳይንሳዊና ዓለም አቀፍ የሆኑ መመሪ ያዎችን በመስጠት የሚረዳ የኢትዮጵያ ደረጃ ምደባ መሥሪያ ቤት መኖሩ ለቃላቱ እጥረት መውጫ አንድ ድጋፍ ነው ። ይህ መሥሪ ሪያ ቤት እስካሁንም ድረስ ብዙ የሳይንስና የሌሎች ጽንሰ ሃሳቦች ትርጓሜዎችን በአማርኛ በመስጠት ብዙ ቃላት ሰብስቦ በማሳተም ላይ መሆኑም ጭምር ታውቋል። ስለዚህ የቋንቋዎች አካዳሚ ይህን ችግር በቅርብ ጊዜ እንደሚፈታው ከፍተኛ ተስፋ የተጣለበት ከመሆ ኑም በላይ ኃላፊነቱንም የሚወስድው መሆኑ የተረጋገጠ ነው። የዩኒ ቬርሲቲው ምሁራን በዚህ አጋጣሚ በመጠቀም በስያሜው ብቻ ሳይ ሆን መጻሕፍቱንም በመድረስ በኩል ታላቅ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ጸሐፊው ይተማመናል ።

## ዋቢ ጽሑፍ ።


1. Bender, M. L, etal. 1976. Language in Ethiopia, London, Oxford University Press.
2. Richter, R. On Language Problems in Ethiopia, (Language Polciy in the Interest of Social Progress) n.d. mimeographed.
3. Tsehaye Teferra, 1977. A Sociolinguistic Survey of Language use and Attitude Towards Language in Ethiopia: Implications for Language Policy in Edicatuon. Ph.D. Dessertation, Georgetown University pp. 163-200.
4. በትምህርት ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ትምህርት አቅጣጫና መመሪያ መጋቢት 1972 አ. አ ገጽ 35.
5. ሙሉጌታ ሥዩም ፤ ስያሜና ችግር ፤ ግንቦት 1972 ዓ.ም ለትርጉም ሴሚናር የቀረበ ጽሑፍ ።